# የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ቦንድ

## 1. ቦንድ ምንድን ነው?

ቦንድ (Bond) እንደ ፕሮሚሰሪ ኖት (Promissory Note) ወይም የግምጃ ቤት ሰነድ የብድር (ዕዳ) መሳሪያ ነው፡፡ ከሌሎች የአጭር ጊዜ የብድር መንገዶችና ከግምጃ ቤት ሰነድ የሚለየው ለረጅም ጊዜ የሚያገለግል በመሆኑ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ቦንድ ልክ እንደ ግምጃ ቤት ሰነድና እንደ ሌሎች የአጭር ጊዜ ክፍያ (Short Maturity) መሳሪዎች ሁሉ በሁለተኛ ገበያ (Secondary Market) ሊተላለፍ የሚችል ፤ ተመልሶ ሊከፈል የሚችል (Redeemable) ፤ ወለድ ሊገኝበትና በአካልም ሆነ በኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ አማካኝነት (Electronically) የሚሸጥ ነው፡፡

## 2.የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ቦንድስ?

የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ቦንድ መንግስት ይፋ ላደረገው የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ የሚውል ገቢ ለማሰባሰብ ሲሸጥ ከቆየው ከኢትዮጵያ መንግስት የቁጠባ ቦንድ ጋር አንድ ዓይነት ዓላማ ኖሮት (እንደ ቁጠባ ቦንድ ሆኖ) በአማራጭነት የቀረበ የቦንድ ዓይነት ነው፡፡ ይህ ቦንድ ዜጎች በአገራቸው ልማት እንቅስቃሴ ላይ ጉልህ አስተዋፅኦ እንዲያደርጉና የራሳቸውንም የቁጠባ ባሕል እንዲያዳብሩ እና የተሻለ የወለድ ምጣኔ እንዲያገኙ የሚያደርግ የቁጠባ ዘዴ ነው፡፡

## 3.የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ቦንድ ጠቀሜታዎቹስ ምንድን ናቸው?

የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ቦንድ ለአገር እንዲሁም ለገዥው በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡

### ለአገር ያለው ጠቀሜታ፡-

- ቁጠባን በማበረታታት ለታላቁ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ የሚውል ገቢ ለማሰባሰብ ያስችላል፤
- በገጠርና በከተማ ከፍጆታ የሚተርፈውንና በባንኮች ያልተሰበሰበውን ገንዘብ ከሕብረተሰቡ በማሰባሰብ ለአገሪቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ መሳካት በዋናነት አስተዋፅኦ ያደርጋል፤
- የጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራትን ገቢ በማሳደግ የአገሪቱን ልማት ያፋጥናል፤
- ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት መንግሥት በግብር መልክ የሚያገኘውን ገቢ እንዲያድግ አስተዋፅኦ ያደርጋል፤
- ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት ተጨማሪ የሥራ ዕድል ይፈጥራል፡፡

### ለገዥው ያለው ጠቀሜታ፡-

- በቦንዱ ላይ የሚከፈለው የወለድ መጠን በንግድ ባንኮች በቁጠባ ሂሳብ ላይ ከሚከፈለው የተሻለ የወለድ ምጣኔ አለው፤
- ቦንድ ገዥው ከገቢው በየጊዜው ገንዘብ እንዲቆጥብ በማድረግ ሀብት እንዲፈጥር ያደርገዋል፤
- የመንግስት ዋስትና ያለው በመሆኑ አስተማማኝ ሰነድ ነው፤
- ቦንድ ከቀረጥ /ከታክስ/ ነፃ የሆነ የወለድ ገቢ ያስገኛል፤
- ከ50 ብር ጀምሮ እስከ ሚሊዮኖች ድረስ መግዛት ይቻላል፤
- ቦንዱን ለገዥው ሕጋዊ ወራሾች እንዲሁም ለሌላ ሁለተኛ ወገን በውርስ ፤ በስጦታ ማስተላላፍ ይቻላል፤
- ቦንዱን በሁለተኛ ገበያ (Secondary market) ለሌላ ሰው ወይም ድርጅት መሸጥ ይቻላልል፤
- እንዲሁም በዋስትና አስይዞ ከባንክ ገንዘብ መበደር ይቻላል፡፡

## 4. ቦንዱን መግዛት የሚችለው ማነው ? ቅድመ ሁኔታዎቹስ?

**ቦንዱን ለመግዛት የተቀመጠ ምንም ዓይነት ቅድመ ሁኔታ የለም፡፡ ማንኛውም ኢትዮጵያዊና ትውልደ ኢትዮጵያዊ ዕድሜ ሳይለይ በተዘጋጀው ፎርም ላይ የገዥውን አጭር መረጃና አድራሻ በማስመዝገብ የሚፈልገውን ያህል ቦንድ መግዛት ይችላል፡፡**

የቀበሌ መታወቂያ ፤ ፓስፖርት ፤ የመስሪያ ቤት መታወቂያ ፤ የልደት ካርድ (ለህፃናት) ፤ የትምህርት ቤት መታወቂያ (ለተማሪዎች) ወይም ማንነትን የሚገልፅ መረጃ በመያዝ ቦንዱን ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ ወይም ከወኪሎቹ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ባንኩ ውክልና ከሰጣቸው ሰባት የብድርና ቁጠባ ተቋማት መግዛት ይቻላል፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖር የውጭ አገር ዜጋ ቦንዱን በብር ወይም በውጭ ምንዛሪ መግዛት ይችላል፡፡ ነገር ግን የቦንዱ ጊዜ ሲያበቃ ገንዘቡ በብር ብቻ ይመለስለታል፡፡

## 5. ቦንዶቹ ሚሸጡት የት ነው?

**ቦንዶቹን፡**

- ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ ዋና መሥሪያ ቤት ፤ ከባንኩ ቅርንጫፎችና ንዑስ ቅርንጫፎች በሙሉ፤
- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ወኪል ሆነው ከሚሰሩት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፎች በሙሉና ባንኩ ውክልና ከሰጣቸው ከደደቢት ፣ ከአማራ ፣ ከኦሮሚያ ፣ ከኦሞ ፣ ከድሬደዋ ፣ ከሐረርና ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ የብድርና ቁጠባ ተቋማት እንዲሁም ወደፊት ባንኩ ውክልና ከሚሰጣቸው የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት መግዛት ይቻላል፡፡

## 6. የቦንዶቹ ዝርዝር መግለጫዎች ምንድን ናቸው?

- አነስተኛው የቦንድ ግዢ መጠን፡ ብር 50.00 (ሃምሣ) ነው፡፡
- ከፍተኛው የቦንድ ግዢ መጠን፡ ጣሪያ ገደብ የለውም
- ቦንዱ የሚከፈልበት ጊዜ (Maturity Period) ከ1 ዓመት እስከ 5 ዓመት

እንዲሁም ከ5 ዓመት በላይ ይሆናል፡፡ ለቦንዶቹ የሚከፈለው የወለድ ምጣኔ ደግሞ፡-

- o ከ1-5 ዓመት ለሆኑ ቦንዶች 5.5 በመቶ (5.5%) ሲሆን
- o የክፍያ ጊዜያቸው ከ5 ዓመት በላይ ለሆኑ ቦንዶች ደግሞ 6 በመቶ (6%) ይሆናል፡፡

- የወለድ ክፍያ ፡ የወለድ ክፍያው በየስድስት ወሩ እ.ኤ.አ ጁን 30 እና ዲሴምበር 31 (በኢትጵያውያን አቆጣጠር ሰኔ 22 እና ታህሳስ 22) ይፈፀማል፡፡

## 7. የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ቦንድን ከክፍያ ጊዜ በፊት መመለስ ይቻላል?

- የክፍያ ጊዜያቸው ከ1-5 ዓመት ለሆኑ ቦንዶች ገዢው ቦንዱን ከገዛበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ ለ1 ዓመት ጠብቆ ለሻጩ ቦንዱን በመመለስ ገንዘቡን መውሰድ ይችላል፡፡
- ክፍያ ጊዜያቸው ከ5 ዓመት በላይ ለሆኑ ቦንዶች ደግሞ ገዢው ቦንዱን ከገዛበት ቀን አንስቶ ቢያንስ 3 ዓመት ጠብቆ ቦንዱን ለሻጩ ተመላሽ በማድረግ ገንዘቡን መውሰድ ይችላል፡፡

## 8. የባለቤትነት ወይም የቦንድ ግዢ ማረጋገጫ ምንድን ነው?

ለቦንድ ገዢ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ (የሽያጭ ቅጽ) በሻጩ ባንክ ወይም ወኪል ተሞልቶ ዋናው ለገዢው የሚሰጥ ሆኖ ኮፒው ፋይል የሚደረግ ሲሆን ገዥው የገዛበትን የገንዘብ መጠን የሚያሳይ ኩፖንም ይሰጠዋል፡፡

## 9. ሌሎች የቦንዱ ገጽታዎች ምንድን ናቸው?

- ቦንዱን ለሚወዱት ወዳጅዎ፣ ጓደኛዎ፣ ልጅዎ ወዘተ. ገዝተው በስጦታ ወይም በውርስ ሊያበረክቱት ይችላሉ፡፡
- ኩፖኑ ቢሰረቅ ወይም ቢጠፋ በ24 ሰዓት ውስጥ ለባንኩ ወይም ለወኪሉ በማሳወቅ በምትክ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት መውሰድ ይችላል ፡፡

**ለቤተሰብዎም ሆነ ለእርስዎ የተሻለ ትርፍ በሚያስገኘው በዚህ አሰራር መቆጠብ ብልህነት ነው**

**የቦንዱ አቅራቢ እና ተጠቃሚ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ**

ይህ አጭር ፅሁፍ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ቦንድ ማስተዋወቂያ ሲሆን ዝርዝር መረጃዎችን ከድረ-ገፃችን መመልከት ወይም በሚከተሉት ስልክ ቁጥሮች በመደወል ማግኘት ይቻላል ፡፡